

❧57-2☙

## ”የሕይወት መሰልቸት”
## (Boredom)
## የሰውን የሕይወት አቅጣጫ ይለውጣሉ

(ካለፈው የቀጠለ)

### 3. ሰው በዕለት ሥራው “መሰልቸት” ሊሰማው ይችላል

ብዙ ሰዎች የተሠማሩበት የሥራ ሞያ ሰለቸን ብለው ሲያማርሩ መስማት አዲስ ነገር አይደለም። በዚህ ምክንያት ብዙ ዘመን ያሳለፉበትን የሥራ መስክ እየለቀቁ ሲወጡ ብዙ ጊዜ እናያለን። “ሁኔታውን ለመለወጥ የምንችለውን ሁሉ አድርገናል፤ ከእንግዲህ ወዲህ አዲስ ነገር እንፈልጋለን” በማለት ሲናገሩ እንሰማለን። ሰዎች በሚሠሩት ሥራ መርካት አቅቶአቸው “መሰልቸት” ሲሰማቸው፥ የሕይወታቸውን አቅጣጫ ለመለወጥ የመጣ ጥሩ ምክንያት ሊሆናቸው ይችላልና ሁኔታውን ለዕድገታቸው መጠቀም መቻል አለባቸው። የብዙዎች በሥራቸው እርካታ ማጣትና መሰልቸት አንደኛውና ትልቁ ምክንያት ከሆኑት በላይ መሆን ስለሚፈልጉ ወይንም ራሳቸውን እንዳሉ መቀበል ስለሚያቅታቸው ይሆናል። በሥራቸው እርካታ የሚሰማቸው ታዋቂነት ያተረፉ ታላላቅ ሰዎች እንጂ “ተራ” ወይንም “መካከለኛ” የሆኑ ሰዎች አይደሉም ብለው ስለሚያምኑ ነው። እዚህ ላይ ማወቅ የሚገባን አራት እውነቶች አሉ፥

1ኛ. በዓለም ካሉ ሥራዎች ውስጥ አብዛኛውን የሚከናወነው “ተራ” በሆኑ ሰዎች ነው። የመጀመሪያው ሰው፥ ማለትም አዳም ከተፈጠረ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በዓለም 30 ቢሊዮን ሰው ወደዚህ ዓለም እንደመጣ አዋቂዎች ይናገራሉ። ከዚህ ከ30 ቢሊዮን ሕዝብ መካከል ታላላቅ ሥራ ወይንም በሰው ዓይን ጎልቶ የሚታይ ነገር የሠሩ ከ5 ሺ እንደማይበልጡ ታሪክ ጸሀፊዎች ይናገራሉ። ይህም ማለት ተደናቂ የሆነ ነገር የሠሩት ከ6ሚሊዮን ሕዝብ መካከል አንድ ሰው ብቻ መሆኑ ነው። ስለዚህ እኔና እናንተ ተደናቂ ባንሆን ተራ የሆነውን የምንሠራ “መካከለኛ” (average) ሰዎች ብንሆን ዝቅተኛነት ተሰምቶን የዕለት ተግባራችን ሊሰለቸን አይገባንም።

2ኛ. ባለን ኀይልና ችሎታ በአቅማችን ማድረግ የምንችለው ሁሉ እስካደረግን ድረስ ሌላውን ሰው ካላከልን በማለት ተስፋ መቁረጥና በምንሠራው ሥራ መሰልቸት አይገባንም። በተሰጠን መክሊት እንደሚገባ መጠቀም ያ፥ የእኛ ኀላፊነት እንደሆነ መርሳት የለብንም (የማቴ. 25፥14-30)። “መካከለኛ” (average) ችሎታ ያላቸው መሆናቸውን የሚያምኑና የተቀበሉ ታላቅ የታሪክ ሰው የነበሩ ሚስተር ቴዲ ሩዝቬልት “መካከለኛ” ችሎታ ስላለው ሰው ሲናገሩ እንዲህ አሉ። “መካከለኛ (average) ችሎታ ኖሮት የተሳካለት ሰው ማለትም መካከለኛ የፖለቲካ ሰው፣ መካከለኛ የሕዝብ አገልጋይ እንዲሁም መካከለኛ ወታደር እነዚህ ሁሉ ድልን የተቀዳጁት በተፈጥሮአቸው በጣም

ብልሆችና ተሰጠ ያላቸው ሆነው ሳይሆን፥ “ተራ” (ordinary) የሆነውን ችሎታቸውን ከተለመደው ወይንም “ተራ” ከሆነው በላይ እንዲሆን ስላዳበሩት ብቻ ነው”።

3ኛ. የእኛ ጥሩ ውጤት የሚለካው ከእኛ በላይ ከሆኑ ሰዎች አቅምና ችሎታጋር በማወዳደር ሳይሆ በራሳችን ደረጃ (አቅም) ልንደርስበትና ልንጨብጠው ከምንችለው ጋር በማስተያየት መሆን አለበት። ራሳችንን ከሌላው ጋር ማወዳደር አንችልም ይሆናል፤ በአቅማችን ለመሥራት የምንችለውን ከመፈጸም ግን ወደ ኋላ ልንል አይገባም። ከአቅማችን በላይ አይጠበቅብንም፣ ከአቅማችን ያነሰ ከሆነ ግን እናንም አያረካንም። ሁለት ወጣት ልጆች አንድ ጊዜ አንድ ማህበር አቋቋሙና የመሰብሰቢያ አዳራሽ ሠርተው ግድግዳው ላይ የማህበራቸውን ሕግና ደንብ ጽፈው ለጠፉ። ጽፈው የለጠፉት ሕግ የልጆች ሥራ ይምሰል እንጂ ከፍተኛ እውነት ያለበት ነበር። ሕጉም የሚለው፥ “በመካከላችን ማንም ትልቅነቱን ወይንም ትንሽነቱን ማሳየት አይችልም፤ ሁሉ መካከለኛ መሆን አለበት” የሚል ነበር። ለማለት የፈለጉት “ሁላችንም ራሳችንን ወይንም የሆንነውን ሆነን መገኘት አለብን” ለማለት ነበር።

4ኛ. “ተራ” (ordinary) የሆነው ነገር “ልዩ” በሆነ ሁኔታ መሥራት አለብን። በእግዚአብሔር ኀይልና ዕርዳታ ልናደርገው የሚያቅተን ነገር አይኖርም። እግዚአብሔር በእኛ ውስጥ ኀይሉን ለመግለጽ፥ ተራውን ነገር ተጠቅሞ ልዩ የሆነ ነገር ይፈጽማል። ታላቁ ዲ. ኤል. ሙዲ በወጣትነት ዕድሜው የታወቀው ሄንሪ ቫርሊክ “ሰው ሕይወቱን ሙሉ በሙሉ ለእርሱ ከሰጠ እግዚአብሔር ለሰውና በሰው የሚያደርገውን አስደናቂ ነገር ዓለም ገና አላየም” ብሎ ሲናገር ሰማው። ይሄ አነጋገር ዲ. ኤል ሙዲን አስደንቆት ማሰብ የጀመረው እንዲህ እያለ ነበር “ሄንሪ ቫርሊ “ሰው” ነው እንጂ ያለው ታላቅ ሰው፣ የተማረ ሰው፣ ሀብታም ሰው፣ ጥበበኛ፣ ሰው የንግግር ችሎታ ያለው ሰው፣ ንቁ ሰው አላለም። ያለው ተራውን ሰው ስለሆነ እኔም ተራ ሰው ነኝና ራሴን ሙሉ በሙሉ ለመስጠት ፈቃደኝነቱ የሚጠበቀው ከእኔው ከራሴ ስለሆነ ያንን ሰው ለመሆን የተቻለኝን ጥረት ሁሉ አደርጋለሁ” አለ። እንግዲህ ማንኛውም “ተራ” ሰው “ልዩ” የሆነው ነገር ለመፈጸም የሚያስችለው ኀይል ቢኖር ይሄ ብቻ ነው። ይህን ካወቀ በሚሠራው ሥራ “ሰልችቶት” ራሱን ከኀላፊነት አያሸሽም።

**4. ሰው ዓላማ ወይንም መመሪያ ሲያጣ “መሰልቸት” ይሰማዋል**

አንዳንድ ሰዎች “የሩቅና” እንዲሁም “የቅርብ” ዓላማ (ግብ) አላቸው። ከግባቸው ለመድረስ ያለመታከት ይለፋሉ። በሕይወታቸው ዓላማ የሌላቸው ሰዎች ዓይናቸውን ጨፍነው እንደሚተኩሱ ሰዎች ናቸው። የሚያነጣጥሩበት ኢላማ ስለሌላቸው ጥይታቸው የትም ይበራል። ዓላማ የሌላቸውም ሰዎች ልክ እንደዚሁ ናቸው። ጳውሎስ ገና ያልደረሰበት ወደፊት ግን ለማግኘት ዓላማ አድርጎ የተነሳው ምን እንደሆነ ሲገልጽ “…የትንሣኤውን ኀይል ለማወቅ በሞቱም እርሱን ለመምሰልና የመከራው ተካፋይ ለመሆን ነው” ይላል (ፊሊጵ. 3፥10)። በሰለጠነው አገር ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች በዓመት አንድ ጊዜ ማለትም በዘመን መለወጫ ዋዜማ ቁጭ ብለው በአዲሱ ዓመት ለማድረግ የሚፈልጉትን ውሳኔያቸውን ያሰፍራሉ። ይሁን እንጂ ከጥቂት ቀን በኋላ ያስተላለፉት ውሳኔ ሁሉ ይረሳል።

መመሪያና ዓላማ ሲኖረን የምንሠራው ሥራ የበለጠ ትርጉም ይኖረዋል፤ ከአሰብነው ዓላማና ግብ ስንደርስ ደግሞ ለደስታ ምክንያት ይሰጠናል። እንዲሁም በሕይወታችን ለሰው

ልጅ ደህንነት ድርሻችንን እንደከፈልን ያረጋግጥልናል። ዓላማ መመሥረትና መጨረሻ ላይ ካሰብንበት መድረስ የምንችለው ጊዜን በአግባቡ በመጠቀምና ራሳችንን "ሥነ ሥርዓት" በማስያዝ ነው። ብዙዎቻችን ግን ቀኑን ለማሳለፍ ብቻ ያለኢላማ ዝም ብለን የምንሮጥ ነን። በሕይወታችን ዕቅድ ስለሌለን ነው እኔና እናንተ በቀላሉ "መሰልቸት" የሚሰማን። የእግዚአብሔር ቃል "በጥንቃቄ ዕቅድ አውጥተህ ብትሠራ ብዙ ሀብት ታገኛለህ፤ ያለዕቅድ በችኮላ ብትሠራ ግን ትደኸያለህ" (ምሳሌ 21፥5) የሚለን ለዚህ ነው። ብዙዎቻችን ጉልበታችንን የሚፈትን አዲስ ነገር የለንም። ለማደግ ከፈለግን ቀኑን ለማሳለፍ ብቻ ከምሯሯጠው የበለጠ መትጋት አለብን። በሕይወታችን ከዛሬ አምስትና አስር ዓመት በኋላ የት ለመድረስ ምን ለማድረግ እናስባለን? መውሰድ ያለብን እርምጃዎች እንዴት ዓይነት መሆን አለባቸው? የእኛን ሥራ ሌሎች ሰዎች እንዲሠሩልን እንጠብቃለን? ከምንፈልግበት ደረጃ ለመድረስ ምን ያህል ዋጋ እንደሚያስከፍለን ተምነናል? በዛሬውን ቀን ምን ለመሥራት ይሆን ዕቅዳችን?

**5. በመንፈሳዊ ሕይወታችን "መሰልቸት" ይሰማን ይሆን?**

ማንኛውም አማኝ ማድረግ ያለበትን እያደረገ በጌታ ውስጥ በማደግ ላይ ከሆነ በመንፈሳዊ ሕይወቱ "መሰልቸት" አይሰማውም ብለን እናምናለን። ይሁን እንጂ ግልጾችና እውነተኞች ሆነን ብንናገር ሁላችንም በሕይወታችን አልፎ አልፎ "የመሰልቸት" ስሜት እንደሚሰማን እንናገር ነበር። ብዙ ጊዜ ይህን ዓይነት ስሜት የሚሰማን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከፍተኛ ነጥብ ላይ ደርሰናንል ብለን በምንልበት ጊዜ ይሆናል። ካለንበት ተነስተን ወደምንፈልገው ደርጃ ለመድረስ ምንም መንቀሳቀስ የማንችልበት "ስልችት" ብሎን በአካባቢያን የማንንም ድምጽ፥ ሌላው ቀርቶ የራሳችንንም ድምጽ እንኳን ቢሆን መስማት የማንፈልግበት ጊዜ አለ።

"ሁልጊዜ በመንፈሳዊ ሕይወታችን ከከፍተኛ ደረጃ ላይ ላንሆን እንችላለን። ማንኛውም ሰው በመንፈሳዊ ሕይወቱ በሁለት ዓይነት ጉዞ ውስጥ ያልፋል። ይኸውም፥ አንደኛው በውስጡ እርሱ ራሱ ለመንፈሳዊ ሕይወቱ ዕድገት የሚያደርገው ጥረት ሲሆን፥ ሁለተኛው ደግሞ በአካባቢው በሚፈጸመው ሁኔታ ምክንያት በውጪያዊው ሕይወቱ ላይ የሚደርሰው ነገር ነው። አስፈላጊውን ጥንቃቄ ካላደርገ፥ ውስጣዊ ሕይወቱን ለመመገብ በውጪ ወይንም በአካባቢው በሚፈጸመው ነገር ብቻ የበለጠ የሚታመን ይሆናል። ለምሳሌ ሃያ አራት ሰዓት ሙሉ በቴሌቪዥን የሚተላለፈውን መንፈሳዊ ፕሮግራም በመከታተል ብቻ ሕይወቱን ለማርካት ይሞክራል። እዚህ ላይ ችግሩ፥ የሚያደርገው ጥረት ሁሉ ውጪያዊ በሆነው ሁኔታ ላይ ብቻ የሚያተኩር መሆኑ ነው። ይሄም እምነቱን የሚያጠምድ እንጂ እምነቱን በሥራ ላይ የሚያውልበት ዕድል አይሰጠውም። ከውጪ መልዕክቱን ይስማው እንጂ ውስጣዊ ሕይወቱን ነክቶ የሚለውጠው አይደለም።

ከመሰልቸት መንፈስ ለማምለጥ እንዳለፉት አንዳንድ መንፈሳዊ አባቶች ሸሽተን በረሃ ወይንም ገዳም መግባት አያስፈልገንም። በውስጣችን የሚሰለቸን ነገር ካለ፥ ያንን አውቀን አቅጣጫችንን እንለውጥ። ነገር ግን ምንም ዓይነት እምርጃ የማንወስድ ከሆነ፥ በጌታ መንግሥት ውስጥ ምንም ዓይነት ተሳትፎ ሳይኖራቸው ዝም ብለው በመቀመጥ እንደሚበሰብሱት አንዳንድ ክርስቲያኖች መሆናችንን ልናውቀው ይገባል።

## 6. ከመሰልቸት ሕይወት የምንወጣበት መንገድ ምን ይሆን?

ኢየሱስ በምድር በነበረበት ዘመን በሕይወቱ “መሰልቸት” ደርሶበት ነበር ብሎ በድፍረት የሚናገር ማንም የለም። የመጨረሻው ሕይወቱ በአገልግሎት የቆየበት ሦስት ዓመት ተኩል እንኳን በብቸኝነት ሕይወት ያሳለፈው አልነበረም። የራሱ ቤተሰብና ህብረት የነበረው ነበር። ኢየሱስ በህይወቱ “መሰልቸት” እንዳይሰማው ምክንያት የሆኑት ነገሮች ለመሆኑ ምን ይሆኑ? ከእርሱ ሕይወት እኔና እናንተ ምን እንማራለርን?

### ሀ. ኢየሱስ ሁልጊዜ ለሰዎች ግድ ነበረው

ኢየሱስ ሰዎች በሚፈልጉት ሰዓት ሁልጊዜ ቶሎ ይደርስ ነበር። ከዳር ቆሞ ሁኔታቸውን የሚመለከት ሳይሆን ፍላጎታቸውንና ትግላቸውን ለማሟላት የሚጥር ነበር (የማቴ. 15፥21-28)። ከመንገዱ ወጥቶ ካሉበት ድረስ መጥቶ እንኳን ያገለግላቸው ነበር። ይህን የሚያደርገው ልቡ በርህራሄና በፍቅር የተሞላ ስለነበረ ነው። እኔና እናንተም በሌሎች ሕይወት ማለት በተጎዱት፣ ችግር ባለባቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ ለውጥ ለማምጣት የምንጥር ብንሆን ምንጊዜም ቢሆን የሕይወት “መሰልቸት” አይሰማንም ነበር። “መሰልቸት” በሕይወታችን ጓዙን ጠቅልሎ ወደ ውስጣችን የሚገባው፥ በራሳችን ፍላጎትና ፍቅር የታሠርን እንደሆነ ነው።

### ለ. ኢየሱስ ሁልጊዜ በእንቅስቃሴ ላይ ነበር

ኢየሱስ የሰዎችን ጥያቄና ፍላጎት ያሟላ የነበረው በፈዘዘ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ አይደለም። የሌለውን መፍጠር ስለሚችል፥ ብዙ ሁኔታዎች እንዲፈጸሙ ያደርግ ነበር (የማርቆ. 1፥32-34)። “ከዚህ ቀጥሎ ምን ያደርግ ይሆን?” በማለት በየቀኑ ብዙዎች ይከተሉት ነበር። ሁልጊዜ ሁኔታዎችንና ሰዎችን ይቀሰቅስ ነበር። እኛም “ከመሰልቸት” ሕይወት ውስጥ ለመውጣት ብንፈልግ፥ ሕይወታችን በእንቅስቃሴ የተሞላ እንዲሆን ማድረግ አለብን። ዝም ባለ ሕይወት ውስጥ መሰልቸት በቀላሉ ሊገባ ይችላል።

### ሐ. ኢየሱስ መልዕክቱን በቀጥታ ያስተላልፍ ነበር

ሊያስተላልፍ የሚፈልገውን መልዕክት ፊት ለፊትና እንዲሁም ሰው ሁሉ ሊገባው በሚችለው ሁኔታ በግልጽ ይናገር ነበር። ንግግሩ በኃይል የተሞላና ሰሚውን ሁሉ የሚቀሰቅስ ስለነበር፥ ብዙዎቹን ጥያቄ እንዲጠየቁና እንዲያስቡ ያደርጋቸው ነበር። ኢየሱስ አድማጮቹን አይመርጥም። ይልቅ ሁኔታን ልክ እንዳለ ወይንም “በአዎንታ” (positive) መልክ ከሚያዩት ሰዎች ጋር ህብረት እንፍጠር።

### መ. ኢየሱስ ማድረግ የሚገባውን ሁሉ ያደርግ ነበር

ከዓላማው ትንሽም ተዛንፎ ወጥቶ አያውቅም። ሰዎችን ወደ ራሱ በመጥራቱ ምክንያት “ስህተት ሠርቻለሁ” በማለት ማንንም ይቅርታ አልጠየቀም። ወደፊት ምን እንደሚጠብቀውና ምን እንደሚያደርግ አስቀድሞ ያውቅ ነበር። ዓላማው ጠፍቶበት የተደነጋገረበት ጊዜ ፈጽሞ አልነበረም። ኢየሱስን “ከመሰልቸት” የጠበቁት ነገሮች ሁሉ እኛንም ይጠብቁናል። ከራሳችን ማምለጥ ካልቻልን፥ ዓላማ የሌለን ከሆንን፣ በሕያአታችን በቀላሉ መሰልቸት ይደርስብናል። ራሳችንን ለሌላው መስጠት ካልቻልን በመንፈሳዊ ሕይወታችን ማደግ አንችልም።

**7. “ከመሰልቸት” ሕይወት ውጪ ለመኖር ብንፈልግ፥**

1ኛ. ሕይወታችንን ብዙ ደስ የሚያሰኙ፥ ስሜትን ሊቀሰቅስ በሚችሉ ጥሩ ጥሩ ነገሮች የተሞላ እንደሆነ አድርገን እንድንመለከት ራሳችንን ማለማመድ አለብን። ሕይወታችንን የበለጠ ጣፋጭ እንዲሆን የሚያደርጉትን ሁኔታዎች እንመልከት። አብዛኛዎቻችን ዓይኖቻችን ወደ ጨለማውና ደብዛዛ ወደ ሆነው ነገር በቀላሉ ስለሚሳብ፥ ሁልጊዜ ሁኔታዎችን የምናየው አጨልመን ነው።

2ኛ. ሁልጊዜ ራሳቸው የጭእፈገጋቸው ሆነው ሁሉንም ነገር አጨልመው ከሚመለከቱ ሰዎች ጋር ብቻ ሕብረት ከመፍጠር ይልቅ፥ ሁኔታን ልክ እንዳለ ወይንም “በአዎንታ” (positive) መልክ ከሚያዩት ሰዎች ጋር ህብረት እንፍጠር።

3ኛ. “ተመችቶናል” ከምንልበት አካባቢ ውጪ ለመውጣት አንፍራ።
አስቸጋሪ ቦታ ነው ከምንለው ሥፍራ ወይንም አካባቢ ለመኖር ራሳችንን እናለማምድ። “ምቾት አለበት” የምንለው ሥፍራ ብዙ ጊዜ ካልተጠነቀቅን የሚያሸራትት ስለሆነ፥ በምቾታችን ስንዝናና አደጋ ላይ እንዳንወድቅ እንጠንቀቅ። ዓይናችን ሁልጊዜ የተከፈተ ይሁን።

4ኛ. “አድጌ አብቅቻለሁ” አንበል። አንዳንዶቻችን አንዴ ያስጨበጡንን ልክ እንኳን ባይሆን መልቀቅ አይሆንልንም። እግዚአብሔር ወደሚያሳየን አዲስ አቅጣጫ ለመመልከት ፈቃደኞች እንሁን። ሁኔታዎች “እንዲሰለቹን” የሆኑበት ዋናው ምክንያት እንድናድግና አቅጣጫችንን እንድንለውጥ ይሆናልና “ለውጥን” አንፍራ።

“መሰልቸት” የምንሠራውን ስናጣ ወይንም ሥራ ፈት ስንሆን የሚሰማን ስሜት ሳይሆን በሥራ ብዛት ስንዋከብ፤ የምንሮጥበት ምክኒያት የሚያጠግብና የሚያረካ መሆኑ አጠያያቂ ሲሆንብንና ሲያጠራጥረን የሚሰማን ስሜት ነው። ዛሬ እኔና እናንተ የማይጨበጠውን “ነፋስ ለመጨበጥ” እንሮጥ ይሆን? በዚህ ዓይነት ሩጫ ውስጥ ከሆንን፥ የምንሠራው ሥራ ብዙ ቢሆንም፥ የመጨረሻው ውጤት ምን እንደሚሆን ግን አናውቅም። ለመሆኑ እኔና እናንተ የምንደክምበት ነገር የመጨረሻው ዋጋው ምን ያህል ነው? ጊዜያዊ ነው ወይንስ ዘለዓለማዊ ብለን ራሳችንን መጠየቅ ይገባናል። ሁኔታዎችን በጥንቃቄ የምንመዝንበትና የምንመረምርበት ፍሬውን ከገለባው ለይተን የምናውቅበት ታላቅ የአዕምሮ ችሎታን እግዚአብሔር ሰጥቶናልና በአግባቡ እንጠቀምበት።

..........................................................................................

በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።